THE EDUCATION STATE

VICTORIA State Government | Education and Training

# (የትምህርት ቤት የግል መረጃ ጥበቃ ፖሊሲ (SCHOOLS' PRIVACY POLICY)

የትምህርት እና ስልጠና መምሪያ (Department of Education and Training) (መምሪያው) ለግል መረጃ ጥበቃ ክብር ይሰጣል፤ ትምህርት ቤቶች የሰበሰቡትን መረጃ ለሦስተኛ ወገን ተላልፎ አይሰጥም፡፡

አማካሪዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ በጎ ፈቃደኞች ጨምሮ ሁሉም የመስሪያቤቱ ሰራተኞች፤ እንዲሁም ሁሉም የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች (**ትምህርት ቤቶች**) የቪክቶሪያ የግል መረጃ ደህንነት ጥበቃ ፖሊሲ ህግና ይህን ፖሊሲ ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

በቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች 'የግል መረጃ' እና 'የጤና መረጃ' አያያዝ የሚመራው *በግል መረጃ ደህንነት እና ጥበቃ መመሪያ (2014* (Vic)) እና *የጤና አመዘጋገብ መመሪያ በግል መረጃ ደህንነት እና ጥበቃ መመሪያ 2014* (Vic) እና *የጤና አመዘጋገብ መመሪያ 2001* (Vic)/ (*Privacy and Data Protection Act 2014* (Vic) and *Health Records Act 2001* (Vic)) ሲሆን (በጋራ **Victorian privacy law**)ተብለው ይጠራሉ)፡፡ በተጨማሪም መምሪያው እና የቪክቶሪያ የመንግስት ትምህርት ቤቶች *የቪክቶሪያ የመረጃ ልውውጥ (**የማጋራት**) መመሪያ 2017 (Victorian Data Sharing Act 2017).*ን ማክበር አለባቸው፡፡

ይህ መመሪያ የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች ከቪክቶሪያ የግል መረጃ አያያዝ ህግ Victorian privacy law እና ሌሎች ተመሳሳይ ደንቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ የግል እና የጤና መረጃዎችን እንዴት እንደሚሰበስቡ እና እንደሚይዙ ይገልፃል፡፡

## የቃላት ፍች

**የግል መረጃ** ማለት ትክክል ይሁን አይሁን ስለ ማንነቱ የሚታይ ወይም ከመረጃው የሚረጋገጥ የአንድ ግለሰብ የተመዘገበ መረጃ ወይም አመለካከት ማለት ነው፡፡ መረጃው ወይም አመለካከቱ በማንኛውም ዓይነት መልኩ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ የግለሰቡ ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና የትውልድ ዘመን (ዕድሜ) የግል መረጃ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

**ልዩ ጥንቃቄ የሚሻ መረጃ** ማለት ከመድልዎ አደጋ ለመከላከል ከፍተኛ የህግ ጥበቃ የሚፈልግ የግል መረጃ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ስለ ተጠቀሰው ግለሰብ ዘር ወይም ጎሳ መነሻ፣ የፖለቲካ አመለካከት ወይም ትስስር፣ የሀይማኖት እምነት ወይም ትስስር፣ የፍልስፍና እምነት፣ ፆታ ወይም ፆታዊ ግንኙነት፣ የተመዘገበ የወንጀል ድርጊት፣ ወይም የንግድ ማህበራት አባል መሆን መረጃ ወይም አመለካከትን ያጠቃልላል፡፡

በቪክቶሪያ የግል እና ልዩ ጥንቃቄ የሚሻ መረጃ *Privacy and Data Protection Act 2014* (Vic).

መሰረት ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

**የጤና መረጃ** ማለት ስለ ተጠቀሰው ግለሰብ አካላዊ፣ አእምሮ ወይም ስነልቦናዊ ጤንነት ወይም ጉድለት መረጃ ወይም አመለካከት ማለት ነው፡፡ የጤና መረጃ ከግል መረጃዎች ዓይነት አንዱ ሲሆን ከተጋላጭነቱ አንፃር የተለያዩ እና ጥብቅ የህግ ጥበቃዎች የሚደረግለት ነው፡፡

በቪክቶሪያ የጤና መረጃ *Health Records Act 2001* (Vic).መሰረት ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

*ማስታወሻ፤* ማንነቱ የተደበቀ የአንድ ግለሰብ መረጃ የግል መረጃ የሚሆነው ተደብቆ የነበረው የግል መረጃ እንደገና እንዲገለጥ ሰደረግ ወይም መረጃው እንደገና ከተገለጠ ሰውየው አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ ለማህበረሰቡ ከተገለፀ ወይም የተሰበሰበው መረጃ አናሳ ከሆነ ነው፡፡

## ምን ዓይነት መረጃ ነው የምንሰበስበው?

ትምህርት ቤቶች የሚከተሉትን የመረጃ ዓይነት ይሰበስባሉ፡፡

- በተማሪዎች፣ በቤተሰቦቻቸው ወይም በሌሎች የሚነገር የተማሪዎች እና የወላጆቻቸው መረጃ - ለምሳሌ አድራሻ እና የትምህርት ምዝገባ ዝርዝር፣ የጤና መረጃ፣ እና የወላጅ እና መድረሻ ሁኔታ፡፡
- በስራ አመልካቾች፣ በመስሪያቤቱ አባላት፣ በበጎ ፈቃደኞች፣ በጎብኝዎች እና በሌሎች የሚቀርብ ስለስራ ማመልከቻ፣ የመስሪያቤቱ ሰራተኞች፣በጎ ፈቃደኞች እና ጎብኝዎች መረጃ - ለምሳሌ የትምህርት ደረጃ፣ ከልጆች ጋር የሰሩ ለመሆናቸው ማረጋገጫ፣ የአስተማሪ ምዝገባ እና የባንክ የግል ዝርዝር መረጃ፡፡
- የተማሪዎች እንቅስቃሴ፣ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች እና በትምህርት ቤቱ የሚካተቱ ከሆነ ቤተሰቦቻቸው (ለምሳሌ በትምህርት ቤቱ CCTV) እይታ ስር ከሆኑ) ወይም የትምህርት ቤቱ ወይም የትምህርት ቤቱ መምሪያ አሰራርን የሚጠቀሙ ከሆነ (እንደ የትምህርት ቤት በይነ-መረብ ወይም የትምህርተ ቤቱን የኮምፒውተር ፕሮግራም) መረጃ፡፡

## ይህን መረጃ እንዴት እንሰበስባለን ?

ትምህርት ቤቶች በተለያየ መንገድ መረጃ መሰብሰብ ይችላሉ ይህም፤

- በግንባር (**በፊትለፊት**) ወይም በስልክ፤ ከተማሪዎች እና ወላጆቻቸው፣ ከመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች፣ ከበጎ ፈቃደኞች፣ ከጎብኝዎች፣ ከስራ አመልካቾች እና ከሌሎች
- ከኢለክትሮኒክስ እና የወረቀት ሰነድ፤ እንደ የስራ ማመልከቻ፣ ኢ-ሜይል፣ ፋክቱር፣ ደብዳቤዎች እና ቅፃቅፆች (እንደ የትምህርት ምዝገባ፣ጉብኝት፣ህክምና፣ የባለሙያ ወይም ፈቃደኝነትን የሚገልፁ ቅፃቅፆች)
- በትምህርት ቤቱ በይነ-መረብ እና ትምህርት ቤቱ የሚቆጣጠረው ማህበራዊ የመገናኛ ዘዴዎች
- በቀጥታ አገልግሎት መተግበሪያ፤ እንደ አፕስ (apps) እና ሌሎች ትምህርት ቤቱ የሚጠቀምባቸው የኮምፒውተር ፕሮግራሞች
- በ ትምህርት ቤቱ በሚገኝ ማንኛውም የእይታ ካሜራ
- በፎቶግራፍ፣ ሲኒማ እና CCTV ሌሎች መመዝገቢያ መሳሪያ
- ከድምፅ መስጫ ቦታ፣ በመረጃ ዳሰሳ፣ በመጠይቅ
- እና አንዳንድ ጊዜም ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በማቀናጀት በተፈቀደ የመረጃ ልውውጥ አገልግሎት

### የመረጃ ማሰባሰብ መግለጫ

በትምህርት ምዝገባ ወቅት እና በየዓመቱ ትምህርት ቤቶች  የመረጃ ማሰባሰብ ሚስጢራዊነት (privacy collection notice) ለቤተሰቦች ያሳውቃሉ (ይህም መረጃ የማሰባሰብ መግለጫ (collection statement) ወይም ሚስጥራዊነት ማሳወቂያ (privacy notice) ተብሎ ይጠራል)፡፡ የሚከተሉት ነገሮችን ያካትታል፤

- ስለ ቤተሰብ እና ተማሪዎች አስመልክቶ መረጃ የመሰብሰቡ ምክንያት
- የመረጃው አጠቃቀም እና አገላለፅ እንዴት እንደሆነ
- እንዴት መረጃውን ማግኘት፣ ማደስ እና ማረም እንደሚቻል

ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጉዳይ ተብሎ የተዘጋጀውን ልዩ የመረጃ ማሰባሰብ መግለጫ በትምህርት ዓመቱ ክፍለ ጊዜ መላክ ይችላሉ፤ ለምሳሌ  አዲስ ቴክኖሎጂ ወይም አሰራር የሚጠቀሙ ከሆነ፡፡

### የፍቃደኝነት መግለጫ የማሰባሰብ ሂደት

የፍቃደኝነት መግለጫ  ማለት አንድ ግለሰብ መረጃ ለመስጠት፣ የተሰበሰበው መረጃ በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ መምሪያ ወይም ከትምህርት ቤቱ ውጭ ለመጠቀም እና/ወይም እንዲሰራጭ ፈቃደኝነቱን ሲስማማ ማለት ነው፡፡

የፈቃደኝነት መግለጫ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተለያየ መንገድ ሊከናወን ይችላል፤ እንደሁኔታው በቃል፣ በቀጥታ መስመር አገልግሎት ወይም በፅሁፍ ሊሆን ይችላል፡፡ ብዛት ያላቸው የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ሂደቶች በትምህርት ዓመቱ ክፍለጊዜ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡

አንዳንድ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ አመታዊ ናቸው፤ ለምሳሌ አመታዊ የፎቶግራፍ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ሂደት፣ አንዳንዱም ለተወሰነ አገልግሎት ብቻ የሚውሉ ሲሆኑ እንደ የትምህርት ቤት ድርጊት መርሃ-ግብር ወይም አዲስ የኮምፒውተር ፕሮግራም  የመሳሰሉትን ለመጠቀም የሚሰበሰብ መረጃን ይመለከታል፡፡

ተማሪዎችን ፎቶግራፍ ለማንሳት የፍቃደኝነት ማረጋገጫ ሲፈለግ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ፎቶግራፍ፣ ሲኒማ እና ምዝገባ ፖሊሲን/ (Photographing, Filming and Recording Students Policy).መተግበር አለባቸው፡፡

በትምህርት ቤቶች የሚከወን የጤና አገልግሎት የተለየ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ቅፃቅፆችን ይጠቀማል፤ ይህም የጤና መረጃን ለመጠቀም እና ለማሰራጨት የፈቃደኝነት ማረጋገጫን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች አገልግሎት መስጫ (Student Support Services) የፍቃደኝነት ማረጋገጫ

### ስለ ሰዎች ጠያቂ የሌለበት (የማይደፈር) መረጃ

ትምህርት ቤቶች ማግኘት ኣለብን ብለው ያልሰሩበት  ስለ እርስዎ መረጃ ሊደርሳቸው ይችል ይሆናል፡፡ በህግ  ከተፈቀደ  ወይም ከተፈለገ ትምህርት ቤቶች ይህን መረጃ ሊይዙት ይችላሉ፡፡ ካልሆነም ፣ ህጉ የሚፈቅድ እና ይህን ለማድረግ አሳማኝ ምክንያት ካለ መረጃውን ሊያጠፉት ወይም ሊያስወግዱት ይችላሉ፡፡

---

## ለምን ይህን መረጃ እንሰበስባለን?

### ስለ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው መረጃ የመሰብሰብ ተቀዳሚ አላማዎች

ትምህርት ቤቶች ስለ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው መረጃ ማሰባሰቡ አስፈላጊነቱ፤

- ተማሪዎችን ለማስተማር
- የተማሪዎችን ማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነት እና ጤና ለመደገፍ
- የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ህጋዊ መስፈርትን ለማሟላት፤
  - በተማሪዎች፣ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች  እና ጎብኝዎች ላይ ለወደፊት ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመት አደጋን ለመቀነስ የሚወሰድ እርምጃ (የጥንቃቄ ተግባር)
  - አካለ ጎደሎ ለሆኑ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር (የመገለል ተፅዕኖን የማይፈቅድ/የሚፀየፍ ህግ)
  - በተቻለ መጠን በትምህርት የስራ ቦታ ላይ የሚገኙ ሰዎች ጤና እና ደህንነት ማረጋገጥ (የስራ ላይ ጤና እና ደህንነት ህግ)
- ትምህርት ቤቶችን ማብቃት፤
  - ከወላጆች ጋር ስለ ተማሪዎች የትምህርት ጉዳዮች ለመወያየት እና የተማሪዎችን ጥረት እና ውጤት ለማክበር
  - የትምህርት ቤቶች ጥሩ ስርዓት እና አያያዝ ለማስቀጠል/ለመጠበቅ
- መምሪያዎችን ማብቃት፤
  - የትምህርት ቤቶች ውጤታማ  የሆነ አያያዝ፣ ተነሳሽነት እና አስተዳደር ለማረጋገጥ
  - በህግ የተሰጣቸውን የስራ ኃላፊነት እና ግዴታ ለማሟላት
  - ዕቅድ ለማውጣት፣ በገንዘብ ለመደገፍ፣ ክትትል ለማድረግ፣ የመምሪያውን ፖሊሲ፣ አገልግሎት እና ስራዎች ለመወሰን እና ለመገምገም
  - የሪፖርት አስፈላጊነት ለማረጋገጥ
  - በትምህርት ቤቶች የሚከሰቱ አጋጣሚዎችን ለማጥናት እና/ወይም መምሪያው እና ትምህርት ቤቶቹን ጨምሮ ለሚቀርብ ማንኛውም ህጋዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት

### ሌሎችን አስመልክቶ መረጃ  ስለመሰብሰብ ተቀዳሚ አላማዎች

ትምህርት ቤቶች ስለ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች፣ ወዶ ዘማቾች እና ስራ አመልካቾች መረጃ የሚሰበስቡት፤

- አመልካቾች ለቅጥር ወይም ለወዶ ዘማችነት ስራ ተስማሚነታቸውን ለማየት
- የቅጥር ወይም የወዶ ዘማች ምደባ ውሳኔ ለመስጠት
- ለመድህን ዋስትና አላማ፤ በድርጅቱ ስራ ምክንያት በማህበረሰቡ ላይ የሚደርስ ጉዳት ካሳ እና WorkCover ያጠቃልላል
- የተለያዩ የህግ ግዴታዎችን ለማሟላት፤ ይህም የቅጥር እና የኮንትራት ግዴታዎች፣ የስራ ላይ ጤንነት እና ደህንነት ህግ እና አጋጣሚዎች ማጥናትን ያጠቃልላል
- ትምህርት ቤቶች ወይም መምሪያውን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ህጋዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት

## መረጃን መቼ እንጠቀማለን ወይም ተደራሽ እናደርጋለን?

መረጃን የመጠቀም እና/ወይም ተደራሽ ማድረግ ማለት እንዴት ለተወሰነ አላማ እንደምንገለገልበት እና ለሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች እንዴት እንደምናሳውቅ እና/ወይም ተደራሽ እንደምናደርግ የሚገልፅ ነው፡፡

ትምህርት ቤቶች መረጃን የሚጠቀሙት ወይም ተደራሽ የሚያደርጉት የቪክቶሪያ የግል መረጃ ደህንነት ጥበቃ ህግ  እና ሌሎች ተዛማጅ ደንቦችን መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

- **ለተቀዳሚ አላማ** - እላይ እንደተገለፀው
- ተቀራራቢ አላማ ላላቸው **ለማጣቀሻነት** ለምሳሌ  የትምህርት ቤቱ አስተዳደር አላማውን፣ ስራውን እና ኃላፊነቱን ለማሟላት እንዲችል
- **ከመግለጫ እና/ወይም የፈቃደኝነት ማረጋገጫ** ጋር  -  ለምሳሌ የትምህርት ምዝገባ ዝርዝር መረጃን ለመጠቀም ወይም ተደራሽ ለማድረግ  የሚፈቅድ የፍቃደኝነት ማረጋገጫ ሲሰጥ (የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ካልተሰጠበት የተሰበሰበው መረጃ ከመምሪያው ውጭ ተደራሽ ማድረግ አይቻልም፤ ተደራሽ ማድረጉ በህግ የተደገፈ ካልሆነ በስተቀር)
- መምሪያው **ትምህርት ለመውሰድ  ወይም ከአደጋ ለመከላከል ይጠቅማል** ብሎ ሲያምን
  - የግለሰብ ሕይወት፣ ጤና፣ ምቾት ወይም ደህንነት
  - የህብረተሰቡ ጤንነት፣ ምቾት ወይም ደህንነት
- **አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ህጋዊነቱ ከተረጋገጠ** -  መድልዎን የሚጠየፍ ህግ፤ የስራ ላይ ጤና እና ደህንነት ህግ፤ የልጆች በጎ አድራጎት እና ደህንነት ህግ፤ የቤተሰብ ሁከት ማስወገድ ህግ፤ ወይም ለድርጅቶች ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ለምሳሌ የጤና መምሪያ እና የቤተሰብ መምሪያ፣ ለቤቶች መምሪያ፤ ለልዩ ፍርድ ቤት እና ችሎት ትዕዛዝ፣ መጥሪያ፣ የክስ መጥሪያ፣ ዋስ፣ የማክበር ወይም መፈፀምን፤ በአንዳንድ አጋጣሚዎችም የመንከባከብ ሃላፊነትንም  ያጠቃልላል

- **በህፃናት እና ቤተሰብ ሁከት ምስክርነት መረጃ ልውውጥ መርሃ ግብር/Child and Family Violence Information Sharing Schemes** አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ በሌሎች የቪክቶሪያ ትምህርት ቤቶች እና የቪክቶሪያዊያን አገልግሎት ስለ ህፃናት በጎአድራጎት ወይም ደህንነት ለማስተዋወቅ፣ ወይም የቤተሰብ ሁከት አደጋን ለማጥናት እና ለመከላከል
- **ህገወጥ** የሆኑ **ተግባራትን** ለማጥናት ወይም ለማስታወቅ፣ ወይም ለተወሰነ **ህግዊ አስገዳጅነት** ላለው አላማ ጠቃሚ ሆነው ሲገኙ፣ ይህም ህግ የመጣስ ወንጀል ወይም አላስፈላጊ የሆነ ተግባር ለማጥናት እና ለመከላከል በህጋዊ ድርጅት ወይም ድርጅቱን ወክሎ የሚሰራ ስራን ያጠቃልላል

- እንደ የግለሰብን መረጃ ሚስጢራዊነት መጠበቅ፣ **ለምርምር ወይም ለትምህርት ቤት መረጃነት** አላማ፣ ወይም የመምሪያውን ፖሊሲ እና ስልት ለማሳወቅ

- **ህጋዊ ጥያቄዎችን** ለመመስረት ወይም ለመመለስ

## ልዩ መለያዎች

ትምህርት ቤቶች ስራቸውን በተቀላጠፈ መንገድ መስራት እንዲችሉ መምሪያው ለእያንዳንዱ የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤት ተማሪ ልዩ መለያ የምዝገባ ስርዓት ሰጥቶአቸዋል፡፡ በተጨማሪም መመሪያው ለእያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠውን ልዩ የቪክቶሪያ ተማሪ መለያ ቁጥር VSN (Victorian Student Number - VSN)  የቪክቶሪያ ስርዓተ-ትምህርት እና ጥናት ባለስልጣን (Victorian Curriculum and Assessment Authority  - VCAA) ተማሪዎች በቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤት፣ ራሳቸውን በቻሉ ሌሎች ወይም ካቶሊክ ትምህርት ቤት ሲመዘገቡ ይጠቀምበታል፡፡ የቪክቶሪያ ተማሪ መለያ ቁጥር (VSN) አጠቃቀም ቁጥጥር ይደረግበታል፤ መጠቀም የሚቻለውም በህግ በተሰጠው ገደብ መሰረት ብቻ ነው፡፡

መምሪያው በተጨማሪም ለዓለም አቀፍ ተማሪዎች የተለየ የዓለም አቀፍ ተማሪ መለያ ቁጥር ሰጥቶአቸዋል፡፡

ሌሎች ትምህርት ቤቶች የተለዩ መለያዎችን  ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

የሞያ ወይም የዩኒቨርሲቲ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ደግሞ በፌደራል መንግስት የታተመው እና በሚከታተለው የተለየ መለያ- ልዩ የተማሪ መለያ (Unique Student Identifier - USI) መዘገባሉ፡፡  ልዩ የተማሪ መለያ (USI) በቀጥታ መስመር አገልግሎት የአውስትራሊያ ስልጠና እና የትምህርት ደረጃ እውቅና ያለው የተማሪ ምዝገባ ለማካሄድ ይጠቅማል፡፡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ወይም ይከታተሉ የነበሩ መሆናቸውን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው  በፊት ልዩ የተማሪ መለያ USI  ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## የተማሪዎች ዝውውር

### በቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል

አንድ ተማሪ ወደ ሌላ የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤት ለመዛወር ቢፈልግ እና ትምህርት ቤቱም ዝውውሩን ከተቀበለው ተማሪው ይማርበት የነበረው ትምህርት ቤት የተማሪውን መረጃ ተማሪው ለተዛወረበት ትምህርት ቤት ማስተላለፍ አለበት፡፡ ይህም የተማሪው የትምህርት መረጃ፣ የጤና መረጃ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ለዚህ ጉዳይ የቤተሰብ ፈቃደኝነት ማረጋገጫ አያስፈልግም፡፡

ይህ አዲሱ ትምህርት ቤት የተማሪውን ትምህርት ለማስቀጠል፣ የተማሪውን ማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነት እና ጤና ለማገዝ እንዲሁም ህጋዊነትን ለመጠበቅ ይረዳልዋል፡፡

### ከ እና ወደ  ቪክቶሪያ የካቶሊክ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች

አንድ ተማሪ  በቪክቶሪያ የሚገኝ መንግስዊ ያልሆነ ሌላ ትምህርት ቤት ለመዛወር ቢፈልግ እና ትምህርት ቤቱም ዝውውሩን ከተቀበለው ተማሪው ይማርበት የነበረው ትምህርት ቤት ከተማሪው የመረጃ  ማህደር የዝውውር ማስታወሻ ከቤተሰብ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ጋር አብሮ ተማሪው ለተዛወረበት ትምህርት ቤት ማስተላለፍ አለበት፡፡

በተጨማሪም የተማሪውን ደህንነት ለመጠበቅ ወይም የቤተሰብ ሁከት ተጋላጭነትን ለማጥናት ወይም ለመከላከል ይረዳ ዘንድ ተማሪው ቀድሞ ይማርበት የነበረው ትምህርት ቤት ለአዲሱ ትምህርት ቤት በመረጃ ልውውጥ ስርዓት መሰረት/( Information Sharing Schemes). መረጃ መስጠት አለበት፡፡

### ከ እና ወደ  ክልል(ግዛት) ትምህርት ቤቶች

አንድ ተማሪ  ከቪክቶሪያ ውጭ ወይም በቪክቶሪያ ወደ የሚገኝ   ትምህርት ቤት ለመዛወር ቢፈልግ እና ትምህርት ቤቱም ዝውውሩን ከተቀበለው ተማሪው ይማርበት የነበረው ትምህርት ቤት የዝውውር ማስታወሻ ከቤተሰብ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ጋር አብሮ ተማሪው ለተዛወረበት ትምህርት ቤት ማስተላለፍ አለበት፡፡

በትምህርት ቤቶች መካከል ለሚደረግ የመረጃ ልውውጥ አስመልክቶ ተጨማሪ መመሪያ በሚከተለው ድህረ-ገፅ ሊገኛሉ ይችላሉ፡፡ https://www2.education.vic.gov.au/pal/enrolment/guidance/student-transfers-between-schools.

## የመመዘኛ ፈተና ውጤት NAPLAN

የመመዘኛ ፈተና NAPLAN ማለት በ3, 5, 7 እና 9 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የማንበብ፣ የመፃፍ፣ የቋንቋ እና ሂሳብ የማስላት ችሎታቸው የሚዳሰስበት ብሔራዊ ፈተና ነው፡፡

ትምህርት ቤቶች የመመዘኛ ፈተና NAPLAN መረጃ ተጠቅመው የሚያስተምሩዋቸው ተማሪዎች ውጤት በመቀመር የትምህርት አሰጣጣቸውን ይገመግማሉ፡፡

የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች የመመዘኛ ፈተና NAPLAN ውጤት ከተማሪዎች የመረጃ ቋት መጠቀም ይችላሉ፡፡ አንድ ተማሪ ከ ኣንዱ ወይም ወደሌላው ራሱን የቻለ፣ ካቶሊክ ወይም የክልል ት/ቤት በወላጅ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ሲዛወር ውጤቱ የተገመገመበት ትምህርት ቤት የተማሪውን የመመዘኛ ፈተና NAPLAN ውጤት ለአዲሱ ትምህርት ቤት መስጠት ይችላል፡፡

## የቅሬታ መልስ አሰጣጥ

የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች እና የመምሪያው ማዕከላዊ እና ክልላዊ ቢሮዎች ከወላጆች እና ሌሎች የቀረበ ቅሬታ ይቀበላሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች እና/ወይም የመምሪያው ማዕከላዊ እና ክልላዊ ቢሮዎች ለቀረቡ ቅሬታዎች መልስ ለመስጠት ትክክለኛ ጊዜ ነው ብለው ሲያስቡ መረጃ ይሰጣሉ፤ (ይህም በሌሎች ድርጅቶች ወይም ወኪሎች የቀረበውን ቅሬታ መልስ መስጠትን ያጠቃልላል)፡፡ ስለ ሂደቱ አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ቅሬታ-የወላጆች ፖሊሲ/(Complaints – Parents policy) ላይ ያገኙታል፡፡ የሚከተለውን ድህረ-ገፅ ይጎብኙ (https://www2.education.vic.gov.au/pal/complaints/policy).

የመምሪያው የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ፕሮግራም ቅሬታዎች (International Student Program - ISP) አስመልክቶ በ ISP ቅሬታዎች እና ይግባኝ ፖሊሲ (Complaints and Appeals Policy) መርህ መሰረት ይስተናገዳል፡፡

(https://www.study.vic.gov.au/Shared Documents/en/School_Toolkit/ISP_Complaints_and_Appeals_Process_Guide.docx).

መምሪያውን ወይም የትምህርት ቤቶች የግል መረጃ አያያዝ ሁኔታን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በግል የመረጃ ሚስጢራዊነት ቅሬታዎች ሂደት መርህ መሰረት ይስተናገዳሉ (https://www.education.vic.gov.au/about/contact/Pages/privacycomplaints.aspx).

## መረጃ ማግኘት

ሁሉም ግለሰቦች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው መረጃ የማግኘት፣ እነሱን አስመልክቶ ትምህርት ቤቱ የሰበሰበው ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃ የማየት መብት አላቸው፡፡ ይህም የሚሆነው መረጃዎችን የማየቱ ተግባር የሕፃኑ ወይም የሕፃናቱን ደህንነት አደጋ ላይ የማይጥል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## የተማሪ መረጃ ማግኘት

ትምህርት ቤቶች ሪፖርት እና የተለመደ የትምህርት ቤት መልዕክት የሚሰጡት ለተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ተንከባካቢዎች ወይም ለዚህ መረጃ ህጋዊ መብት ላላቸው ብቻ ነው፡፡ የሌሎች ተማሪዎች መረጃ የማግኘት ጥያቄ በመረጃ የማግኘት ነፃነት (Freedom of Information - FOI) መተግበሪያ በመምሪያው Freedom of Information ክፍል በኩል ይሆናል፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች ውክልና ያለው ሰው የተማሪ መረጃን ማየት ላይፈቀድለት ይችላል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤ የተሰጠው ውክልና በተማሪው መልካም ፈቃድ ካልሆነ፣ የእኛን የተማሪ እንክብካቤ ሃላፊነት የጣሰ ከሆነ፣ ከአናሳ ብሔረሰብ የተገኘ ታዳጊ ፍላጎት የሚፃረር ከሆነ ወይም ምክንያታዊ ያልሆነ የሌላውን ሰው የግል ነፃነትን የሚጋፋ ከሆነ፤

በተጨማሪም Child and Family Violence Information Sharing Schemes የህፃናት በጎአድራጎት ወይም ደህንነት ለማሳወቅ ወይም የቤተሰብ ሁከት አደጋን ለማጥናት እና ለመቆጣጠር ይረዳ ዘንድ የተወሰኑ ድርጅቶች እርስ በእርስ ሚስጥራዊ የሆነ መረጃን መለዋወጥ እንዲችሉ ይፈቅዳል፡፡

የቪክቶሪያ ትምህርት ቤቶች እና የተለያዩ ሌሎች የቪክቶሪያዊያን አገልግሎቶች በዚህ ስር ይመደባሉ፡፡ለበለጠ መረጃ (Information sharing and MARAM reforms) ይመልከቱ (https://www.vic.gov.au/information-sharing-schemes-and-the-maram-framework).

## የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞችን መረጃ ማግኘት

የትምህርት ቤት ሠራተኞች የግላቸው የሆነውን የስራ ማህደር ርዕሰ መምህሩን በማስፈቀድ ማየት ይችላሉ፡፡

የሰራተኞች የጤና መረጃ መመሪያን ለማግኘት (Access to health information – Employees) ይመልከቱ (https://www2.education.vic.gov.au/pal/access-health-information/overview).

በቀጥታ የማግኘቱ ፈቃድ ከሌለዎት የመስሪያ ቤቱ አባል የሆነ በሚከተለው ሁኔታ በመምሪያው (Department's) Freedom of Information Unit.በኩል ሊረዳዎት ይችላል፡፡ ለበለጠ መረጃ Freedom of information መጠየቂያን(requests )ን ይጎበኙ (https://www.education.vic.gov.au/about/working/Pages/foi.aspx)

## መረጃ ማከማቸት እና ደህንነቱን መጠበቅ

የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች መረጃን ከአግባብ ውጭ መጠቀም፣ ማጥፋት፣ላልተፈቀደለት ሰው ማሳየት፣ መለወጥ እና መግለፅን ለመከላከል ምክንያታዊ የሆነ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ሁሉም የወረቀት እና የኢለክትሮኒክስ መረጃዎች በ መምሪያው መረጃ አያያዝ ፖሊሲ እና የመረጃ ደህንነት ደረጃዎች መሰረት በጥብቅ ቦታ ይቀመጣሉ፡፡ የቪክቶሪያ የህዝብ መዛግብት ቢሮ መረጃ ማከማቻ እና ማሰራጫ ባለስልጣን Retention and Disposal Authorities. በሚያዘው መሰረት ሁሉም የትምህርት መረጃዎች ተገቢ በሆነ ቦታ ይቀመጣሉ ወይም ለመንግስት መዝገብ ቤት (ለቪክቶሪያ የህዝብ መዛግብት ቢሮ) (State Archives - Public Record Office Victoria), ተላልፈው ይሰጣሉ፡፡ ለበለጠ መረጃ (Records Management policy for schools) ይመልከቱ፡፡

የቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤቶች በመረጃ ሚስጢራዊነት እና መረጃ አያያዝ ችግሮች ላይ የተሰማሩ የኮምፒውተር ፕሮግራም እና የኮንትራት አገልግሎት ሰጪዎችን ለማግኘት ይረዳቸው ዘንድ የአጠቃቀም መመሪያ እና መረጃ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት የግል መረጃ ለመያዝ ፣ ጥብቅ ወይም የጤና መረጃ ለመያዝ የተጠቀሙበት የሦስተኛ ወገን የኮምፒውተር ፕሮግራምን ለመገምገምሚስጢራዊነት ያመጣው ለውጥ ግምገማ (PIAs). (Privacy Impact Assessments - PIA) ይረዳቸዋል፡፡ PIAs ማካሄድ ትምህርት ቤቶች የሚስጢራዊነት እና ደህንነት ጥበቃ

አደጋዎችን ለመለየት፣ የቪክቶሪያ የሚስጢራዊነት ጥበቃ ህግ ጋር የሚስማማ መሆኑን ለመገምገም፣ የተለዩ አደጋዎችን ለመቆጣጠር የሚያስፈልጉ ድርጊቶችን ለመዘገብ ይረዳል፡፡

የአውሮፓ ሕብረት European Union’s (EU’s) የወል መረጃ ጥበቃ ህግ(GDPR) (General Data Protection Regulation - GDPR) ከ EU በመጡ የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ

ይሆናል፡፡ ለተጨማሪ ጥያቄ international@education.vic.gov.au ይጎብኙ

## መረጃዎን ማሻሻል/ወቅታዊ ማድረግ

ስለ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች የምንይዘው መረጃ ትክክለኛ፣ ሙሉዕ እና ወቅታዊ መሆኑ ጠቃሚ ነው፡፡ እርስዎ የሰጡአቸው መረጃ ከተለወጠ እባክዎን የትምህርት ቤቱን ዋና ቢሮ ያነጋግሩ፡፡

## መረጃ የማግኘት ነፃነት እና ሚስጢራዊነት (FOI)

ወደ FOI ለማመልከት ሲሹ የሚከተለውን አድራሻ ይጠቀሙ:

**Freedom of Information Unit**
**Department of Education and Training**
**2 Treasury Place, East Melbourne VIC 3002**
**(03) 7022 0078**
foi@education.vic.gov.au
መረጃ የማግኘት ነፃነት አስመልክቶ የበለጠ መረጃ ሲፈልጉ https://www.education.vic.gov.au/about/working/Pages/foi.aspx. ድህረ-ገፅን ይመልከቱ

የመረጃ ሚስጢራዊነት አስመልክቶ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ካለዎት እባክዎን የሚከተለውን አድረሻ ይጠቀሙ

**Knowledge, Privacy and Records Branch**
**Department of Education and Training**
**2 Treasury Place, East Melbourne VIC 3002**
**(03) 8688 7967**
privacy@education.vic.gov.au